# የ ቤት ውስጥ አገልግሎቶች ኢንዱስትሪ-የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኞች:: የኮቪድ-19 መስፈርቶች፡፡

ይህ ሰነድ ለአገር ውስጥ የአገልግሎት ኢንዱስትሪ እና በተለይም ለቤት እንክብካቤ ሠራተኞችም ነው ፡፡ ለዚህ ሰነድ ዓላማ ፣ የ ቤት ውስጥ አገልግሎት ሠራተኛ ማለት በ አንድ ወይም ከዚያ በላይ አሰሪዎች የሚከፈለው እና በግል መኖሪያ ቤት ውስጥ እንደ የ ቤት ሠራተኛ የ ቤት ውስጥ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ማንኛውም ሠራተኛ ነው ፡፡ የ ቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞች የ ሰዓት ተከፋዮች እና ደመወዝ ተከፋይ ፣ የ ግል ሥራ ተቋራጮችን ፣ የሙሉ ሰዓት፤የትርፍ ሰዓት ሠራተኞችን እና ጊዜያዊ ሠራተኞችን የሚያካትት ገለልተኛ ተቋራጮች ያካትታል ፡፡ አሠሪ ማለት የ ቅጥር አካላትን ፣ ግለሰቦችን ፣ ቤቶችን እና አሠሪዎችን ያጠቃልላል (ለምሳሌ ፣ ቀጥታ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የንግድ ሥራ ድርጅቶችን እና ኦንላይን አማራጮችን ጨምሮ) የቤት ሠራተኛ አገልግሎቱን በቤት ውስጥ የሚሰጠውን አገልግሎት በቀጥታ ወይም በ ተዘዋዋሪ ይከፍላል ፡፡ ከ አንድ በላይ አሠሪ በሚኖርበት ጊዜ ለእያንዳንዱ አሠሪ / ሠራተኛ የሥራ ስምሪት ግንኙነት ግዴታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ ፡፡

ሌሎች የ ቤት ውስጥ ሠራተኞች በተለየ መመሪያ የሚጠቃለሉ ሲሆን በአስተዳደሩ አዋጅ 20-05 መሠረት ግን ስራቸው ስጥ ሠራተኞች በተለየ መመሪያ የሚጠቃለሉ ሲሆን በአስተዳደሩ አዋጅ 20-05 መሠረት ግን ስራቸው አስፈላጊ ነው ተብሎ አልተጠቀሰም ፡፡ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኞች ፣ በግል ወይም በቤት ውስጥ ፣ የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ዜጎች ፣ ወይም ለታመሙ ፣ ለአረጋውያን ወይም ተጋላጭ ለሆኑ ግለሰቦች የዕለት ተዕለት የኑሮ እንቅስቃሴዎቻቸውን ይደግፋሉ ለምሳሌ ማብላት ፣ማጠብ እና ማልበስ፡፡ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኛ በዕለት ተዕለት የኑሮ እንቅስቃሴዎች ላይ ከማገዝ በተጨማሪ ግለሰቦች በኅብረተሰቡ ውስጥ ራሳቸውን ችለው ለመኖር የሚያስችሏቸውን "የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን" ሊረዱ ይችላሉ ፡፡ የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኞች በክልል የጤና ክፍል እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዕውቅና Department of Health ግን አይገደብም RCW 18.88B.

በ ቤት ውስጥ እንክብካቤ የሚሰሩ ሠራተኞች በአስተዳደሩ አዋጅ 20-05 መሠረት አስፈላጊ ሠራተኞች ተደርገው ተመድበዋል ስለሆነም በ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ አማካኝነት ብዙ አገልግሎቶች እንዲቀጥሉ ተደርገዋል ፡፡ የጤና እና ደህንነት መስፈርቶች በአሠሪዎች እና በተራ ግለሰብ የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኞች በተመዘገቡት መሠረት ተፈጻሚ መሆን አለባቸው ፡፡

*ማናቸውም ድንጋጌዎች ለአንድ ነጠላ ሠራተኛ አሠሪ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ የማይውል እስከሆነ ድረስ እንደዚህ ባለ አሠሪ መከተል የለበትም ፡፡*

በ አገር ውስጥ የኢንዱስትሪ አገልግሎት ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች ሥራቸውን ለማከናወን ፣ የሕመም እረፍት ከከፍያ ጋር እና የሥራ አጥነት ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት አቅም ውስንነቶች እንደሚያጋጥማቸው እውቅና ተሰጥቶታል ፡፡ በሁሉም የሥራ ሁኔታዎች፤ አሠሪዎች የሠራተኞቻቸው ለአደጋ ተጋላጭነት በመከላከል ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን ውስንነት ማወቅ አለባቸው ፡፡

**የደህንነት እና የጤና መስፈርቶች፡፡**

ሁሉም የ ቤት ውስጥ አሠሪዎች በ ክልል እና በፌዴራል ሕግ እና ደንቦች መሠረት ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የሥራ ቦታን የመፍጠር አጠቃላይ ግዴታ አለባቸው ፡፡ በተጨማሪም ፣ "Safe Start" አዋጅ 20-25.4 በተደነገገው የሚከተሉትን የ ኮቪድ-19 የስራ ቦታ-ተኮር የደህንነት ልምዶች ማክበር ግዴታ አለባቸው L&I ፡፡ ለሥራ ቦታዎች አጠቃላይ መስፈርቶች እና የመከላከያ ሀሳቦች. የዋሽንግተን ስቴት የጤና ክፍል እና የዋሽንግተን ስቴት ማኅበራዊ እና የጤና አገልግሎቶች ክፍል ለሠራተኞች የደኅንነት መመሪያ ሰነዶችን አዘጋጅተዋል::

- የዋሽንግተን ግዛት የጤና ክፍል ምክረ ሐሳብ ለቤት ውስጥ እንክብካቤ አቅራቢዎች፡፡
- የዋሽንግተን ስቴት የማኅበራዊ እና የጤና አገልግሎቶች ክፍል አቅራቢዎች (IPs) በ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት ደህንነቱ የ ተጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት መመሪያ ማወጣት፡፡

እንደ የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ኤጀንሲዎች እና የዋሽንግተን ስቴት ያሉ አስተዳደራዊ ተግባሮችን የሚያከናውን አሠሪ ወይም የሥራ አሠሪ ሠራተኛን ጨምሮ የ ኮቪድ-19 መስፈርቶችን እና መመሪያዎችን መከተል አለበት ፡፡

- ስለ ኮሮና ቫይረስ እና ስርጭቱን እንዴት መከላከል እንደሚቻል እና የአሠሪውን የኮቪድ-19 ፖሊሲዎች በተሻለ መልኩ በሚረዱት ቋንቋ ያስተምሯቸው።
- በተቻለ መጠን ያህል በሰራተኛውና በደንበኛው መካከል ስድስት ጫማ ርቀት መኖር አለበት፡፡ ለአንድ የተወሰነ ሥራ ጥብቅ አካላዊ ርቀትን መጠበቅ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ሌሎች ዘዴዎችን እንደ ቦታዎችን መከለል ፣ ሰራተኞችን ወይም ደንበኞችን በጠበበ ወይም በተጨናነቁ አካባቢዎች ቁጥሩን መቀነስ ፣ እና የ ዕረፍት ጊዜ እና የሰራ ፈረቃ መጀመሪያ ሰአትን ሰራተኛው ራሱ በሚመቸው ጊዜ እንዲወስን ማድረግ የመሳሰሉ እና ሌሎች የመከላከያ እርምጃዎች ስራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

- ለሠራተኛው ያለ ምንም ወጪ ተገቢውን የእጅ መከላከያ ፣ ጓንት ፣ የፊት መከላከያ እና የፊት ጭንብል ያሉ የ ግል መከላከያ መሳሪያዎችን (PPE) ማቅረብና እንዲለብሱ ማድረግ ፡፡ ለተጨማሪ ዝርዝሮች የኮሮና ቫይረስ የፊት መሸፈኛ እና ጭንብል መስፈርቶችን ይመልከቱ። በኮቪድ የተያዙ ወይም ምልክት ላላቸው ደንበኞች እንክብካቤ የሚያደርጉ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰራተኞች "እጅግ በጣም ከፍተኛ አደጋ" ውስጥ እንደሆኑ በመገንዘብ እና PPE መሰጠት አለባቸው። የበሽታውን ምልክት ለማያሳዩ ደንበኞችን እንክብካቤ የሚሰጡ የቤት ውስጥ ሠራተኞች በ "መካከለኛ አደጋ" ምድብ ውስጥ እንዳሉ ማወቅ አለባቸው እንዲሁም እንደየሁኔታው ተገቢ የሆነ ተጨማሪ PPE ማቅረብ ያስፈልጋል. በተጨማሪም የ ጨርቅ የፊት ሽፋኖች በአሠሪዎች መሰጠት አለባቸው እናም በሁሉም ሰራተኛ መደረግ አለባቸው ይህ ግን ለብቻቸው የሚሰሩ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ተግባሮችን ሲያከናውን የእነሱ ተጋላጭነት በሠራተኛ እና ኢንዱስትሪዎች ደህንነት እና የጤና ሕጎች እና መመሪያዎች መሠረት ከፍተኛ ጥበቃን የሚያመጣ ካልሆነ በስተቀር መደረግ አለበት ፡፡ የ ጨርቅ የፊት መሸፈኛ በ ጤና መመሪያ ውስጥ ተገልጿል። የ ጨርቅ የፊት ሽፋን ማድረግ ከማያስፈልግባቸው መስፈርቶች ውስጥ በ ቢሮ ፣ በመኪና ፣ ወይም በሥራ ቦታ ብቻዎትን ሲሠሩ፡፡ ግለሰቡ መስማት የተሳነው ወይም የመስማት ችግር ካለበት እና ከ ሌላ ሰው ጋር ለመግባባት የፊት አመልካቾች ፣ የንግግር እና የአፍ እንቅስቃሴዎች እንደ የ ንግግር አካል ያሉ የ ቋንቋ ምልክቶች ከሚጠቀም ሰው ጋር የሚገናኝ ከሆነ ፣ ግለሰቡ የፊት መሸፈኛ መጥቀም አግባብነት የለውም፡፡ የጤና ሁኔታ ወይም የአካል ጉዳት ካለበት ፤ ወይም ሥራው በ አካል ውስጥ ጣልቃ የማያስገባ ከሆነ።

አሠሪው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ ሠራተኞቹን ለመጠበቅ የ ኮቪድ-19 መስፈርቶችን እና መመሪያዎችን መከተል አለበት ፡፡ የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኞች በተናጥል ሸማቾች የተቀጠሩና በ DSHS በኩል ክፍያ የከፈሉ እንደ አቅራቢዎች እንደ ተመረጡ ፣ በፕሮግራሙ ተይዘው በደንበኞች አሠሪ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል ፡፡ በ እነዚህ አጋጣሚዎች ፣ DSHS ኢንፌክሽኑን እንዴት መከላከል እና ስርጭቱን መግታትን በ ተመለከተ መመሪያ ይሰጣል፡፡

- አዘውትረው እና በ በቂ ሁኔታ የእጅን መታጠቦን ያረጋግጡ፤ በቂ የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት መኖሩንም ያረጋግጡ፡፡ በ መሣሪያ ወይም በሌሎች በጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ላይ የቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል እንዲረዳ የሚጣሉ ጓንቶችን ይጠቀሙ ፡፡
- በተለምዶ አዘውትሮ የሚነኩ ቦታዎችን ማፅዳቶን ያረጋግጡ ፡፡
- በስራ ሽፍት መጀመሪያ ላይ ሁሉንም ስራተኛ ወይም ደንበኛ የኮቪድ-19 ምልክቶችና ስሜቶች መኖራቸውን ይፈሹ፡፡ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኞች ከታመሙ ወይም የህመም ስሜት ከተሰማቸው ቤት መቆየት ወይም ወዲያውኑ ወደ ቤት መሄድ አለባቸው ፡፡ በኮቪድ-19 የ ተያዘ ወይም የ ተጠረጠረ ስራትኛ ሲገኝ፣ የነበረበትን ቦታ ወይም ቢሮ በመዝጋት የነካቸውን ቦታዎች፣ ሲስራባቸው የነበሩ ቦታዎችን በደንብ ማጽዳት ያስፈልጋል፡፡ በደንብ ላማጽዳትና ሳኒታይዝ ለማድረግ በበሽታ መቆጣጠሪያ ማእከሎች የተቀመጡትን የጽዳት መመሪያዎች ይከተሉ ፡፡
- አሠሪው ስራኛው ከ ሥራው ባህሪ የ ተነሳ በኮቪድ ከ ተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት እንዳለው ሲያረጋግጥ ወዲያውኑ ለቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኞችው ለበሽታው መጋለጡን ማሳወቅ አለበት ፡፡

አንድ ሰራተኛ በ ኮቪድ-19 የተፈጠሩ አደጋዎችን ጨምሮ ደህንነታቸው ያልተጠበቁ ስራዎችን ላለመስራት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል ፡፡ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኛ ሰዎቹ ያሉበት ሁኔታ ጥሩ ነው ብሎ ካላመነ የማህበራዊ ሰራተኛን ወይም የኤጀንሲውን ተቆጣጣሪ ማሳወቅ አለበት፡፡ በRCW 49.17 ማእቀፍ ስር የሆነ ማንኛውም አሠሪ በሥራ ላይ እምቢታውን ለገላጸ በደህንነት ጥበቃ ሥራዎች ላይ የተሰማራ ሠራተኛ የተወሰኑ መስፈርቶችን የሚያሟላ ከሆነ በሕጉ መሠረት እርምጃ መውሰድ ሕገወጥ ነው ፡፡ መረጃ በ እነዚህ ሕትመቶች ውስጥ ይገኛል: የደኅንነት እና የጤና መድልዎ በስራ ቦታው ብሮሹር እና በስፓኒሽኛ የደህንነት እና የጤና መድልዎ ብሮሹር.

ለኮቪድ-19 የመጋለጥ ሥጋት አድሮባቸው እራሳቸውን ከሥራ ቦታ ለማራቅ የመረጡ ሰራተኞች የተወሰኑ የሥራ ፈቃድ ወይም የሥራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች ሊኖራቸው ይችላል ፡፡ ተለዋጭ የሥራ አደረጃጀት የማይቻል ከሆነ አሠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 20 -46 የሚሸፈኑ ለአደጋ የተጋለጡ ግለሰቦችን በፈቃዳቸው የተጠራቀመ የአመት እረፍት ወይም የሥራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ ሌሎች ሠራተኞች በቤተሰቦች የህመም ታሪክ፣ የኮሮናቫይረስ መከላከል አቅም ፣ የሥራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች ወይም በሌሎች ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ የተዘረጉ የቤተሰብ እና የህክምና ፈቃድ ማግኘት ሊችሉ ይችላሉ ፡፡ ተጨማሪ መረጃ በ ኖቬል ኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ (ኮቪድ-19) ግብዓቶች ወይም በዋሽንግተን የ ቤተሰብ እንክብካቤ ሕግ እና በቤተሰቦች የመጀመሪያ ኮሮናቫይረስ ምላሽን መሠረት የሚከፈለው ክፍያ ይገኛል

**<u>የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኞች፡፡</u>**

በተጨማሪም ሠራተኞች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው: -

1. ከታመሙ በቤትዎ ይቆዩ ፡፡ በ ኮቪድ መያዙ ከተጠረጠረ ወይም ሲረጋገጥ አሠሪዎን ያሳውቁ ፡፡
2. በኮቪድ-19 የታመመ የቤተሰብ አባል በቤት ውስጥ ካለ አለቃዎን ያሳውቁ፡፡ አንድ ሠራተኛ በ ኮቪድ-19 የታመመ የቤተሰብ አባል ካለው ፣ ያ ሠራተኛ በክልሉ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተቋቋመው የራስን ማግለል መስፈርቶችን መከተል አለበት።
3. ወደ ሥራ ከመመለሶ በፊት ደውለው ይንከባከቡት የነበረው ሰው አዲስ የሆነ ትኩሳት ፣ ሳል ፣ የ ትንፋሽ እጥረት ምልክቶች እያጋጠመው እንደሆነ ይጠይቁ ፡፡ እንደዛ ከሆነ ፣ በ ኮቪድ-19 የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰነድ ውስጥ የተዘረዘሩ አገልግሎቶች ላይ በመመርኮዝ ሊዘገዩ ወይም ሊፈጸሙ የሚችሉ አገልግሎቶች ከግምት ያስገቡ ፡፡

4. ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር ሁል ጊዜ በቤት ውስጥ በእርሶ እና በሌሎች መካከል ቢያንስ ስድስት ጫማ ርቀት መኖር ይገባዋል ፡፡ አካላዊ ርቀትን ለአንድ የተወሰነ ሥራ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ሌሎች የ መከላከያ እርምጃዎች እንደ የ ጨርቅ የፊት መሸፈኛዎች እና PPE መጠቀም አለቦት.
5. በስራ ሰዓት መጀመሪያ እና መጨረሻ እንዲሁም ምግብ ከማዘጋጀትዎ በፊት እና በኋላ እንዲሁም ከ ሰውነት ፈሳሽ ጋር ንክኪነት ካሎት ደጋግመው እጅን ይታጠቡ ይኑሩ ፡፡ እጅዎን በሳሙና እና በውሃ ቢያንስ ለ 20 ሰከንዶች ይታጠቡ ወይም ቢያንስ 60% አልኮል የያዘ የእጅ ማጽጃ ይጠቀሙ።
6. በተቻለ መጠን በ ቤት ውስጥ ያሉትን ነገሮች ወይም እቃዎችን ከመንካት ይቆጠቡ ፡፡ በሚሰሩበት ጊዜ በ ተደጋጋሚ የነኩትን ቦታዎች በደንብ ይጠቡ ፡፡

<u>**በራሳቸው ቤት ውስጥ አገልግሎት ለመስጠት የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኛ የሚቀጥሩ ግለሰቦች:**</u>

7. ደንበኛው በ ቤት ውስጥ ራሱን ካገለለ ፣ ሕመም ወይም ከ ኮቪድ-19 ጋር የሚዛመዱ ምልክቶችን በሚዳብርበት ጊዜ የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሠራተኛውን ያሳውቁ ፡
8. የ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ሠራተኛ ከ ታመመ ፣ እስኪሻላቸው ድረስ ስራ እንዳይሠሩ ይጠይቋቸው ፡፡
9. የ ቤት ውስጥ ተንከባካቢ በሚኖርበት ወቅት እጅን አዘውትረው ይታጠቡ ፡፡
10. ከአቅም በላይ ካልሆነ ከቤት እንክብካቤ ሰጪ ባለሙያው ቢያንስ ስድስት ጫማ ርቀት ይኑርዎት እና ከባለሙያው በቅርብ ርቀት መስሪያ ጊዜን ያሳንሱ።

<u>***የሥራ ቦታ መመሪያዎች፡፡***</u>

11. በ ቤት ውስጥ እንክብካቤ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ጭምብል ማድረግ እና ማናቸውም ሰው በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳይሰራጭ ለመከላከል ቢያንስ በጨርቅ ፊትን መሸፈን አለበት ፡፡ እንደነዚህ ያሉት ግለሰቦች ሁሉንም የ PPE መስፈርቶችን እንዲከተሉ አጥብቀው ይበረታታሉ ፡፡ በሚቻልበት ጊዜ በ ቤት ውስጥ ያሉ ሰዎች በ ቤት ውስጥ ከሚሰራው ሰው ርቀታቸውን መጠበቅ አለባቸው፡፡ወይም ከትናንሽ ክፍሎች ወደ ትልልቅ ክፍሎች በመሰደድ አካላዊ ርቀትን መጠበቅ አለባቸው ፡፡ በስነ-ልቦና ፣ በ እድገት ወይም በስራ ጉድለት የ ተነሳ በስራ ቦታ ላይ ያሉ ግለሰቦች ለህጉ መገዛት አይችሉም ፣ መገዛትም አይጠበቅባቸውም ፣ በግንዛቤ ፣ በእድገት ወይም በሥራ እክል ምክንያት የ ጨርቅ ሽፋን እና / ወይም PPE አይጠቀሙም።
12. ከሰዎች ጋር ያሎት ግንኙነት አጭር ይሁን። አስፈላጊ ዝርዝሮችን በአካል ሳይገናኙ ለመወያየት ካልቻሉ የግንኙነትዎን ጊዜ ያሳጥሩ እና በማንኛውም ጊዜ የስድስት ጫማ ርቀትን ይጠብቁ ፡፡ በስነ-ልቦና ፣ በ እድገት ወይም በስራ ጉድለት የ ተነሳ በስራ ቦታ ላይ ያሉ ግለሰቦች ለህጉ መገዛት አይችሉም ፣ መገዛትም አይጠበቅባቸውም ፣ በግንዛቤ ፣ በእድገት ወይም በሥራ እክል ምክንያት የ ጨርቅ ሽፋን እና / ወይም PPE አይጠቀሙም።
13. ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በስራ ቦታ ወይም በ ቤት ውስጥ መቅረብ አለባቸው ፡፡
14. አሠሪዎች ሰራተኞቻቸው ደህና ነው ብለው ካላመኑ እራሳቸውን ከሥራ ቦታ የ ማስወገድ መብታቸው እንደሆነ እንዲሁም በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የ አመት እረፍት ወይም የሥራ አጥነት ጥቅማጥቅሞችን ለሠራተኞቹ ያሳውቃሉ ፡፡
15. የቤት ሰራተኛ ተጨማሪ ስራእንደ ተደጋጋሚ የጽዳት ስራ መስራት የሚጠበቅበት ከሆነ ይህ በ ጽሑፍ ስምምነት ውስጥ መካተት ያለበት እና ሰራተኞች ለሰሩት ስራ ማካካሻ ሊከፈላቸው ይገባል
16. ሁሉም ስልጠና ለመስከ ሰራተኞች መከናወን ያለበት በክፍያ ወቅት ነው፡፡
17. ሁኔታዎች የሚፈቅዱ ከሆነ ሠራተኞች በተናጥል በማሽከርከር ወደ ሥራ ቦታዎች መሄድ አለባቸው፡፡በአንድ መኪና አንድ ሰው ብቻ ፡፡
18. ሰራተኞች በአማካኝ ቦታ ተሰብስበው በኩባንያው ተሽከርካሪዎች ወደ ሥራ ቦታ የሚጓዙ ከሆነ ፣ አንድ ተሽከርካሪ ለአንድ ይመድቡ እና አይቀያይሩዋቸው ፡፡ በኩባንያው ባለቤትነት በተያዙ ተሽከርካሪዎች ወይም በሌላ ባለብዙ ተሳፋሪ ተሽከርካሪ ውስጥ መጓዝ በተጠቀሰው መሠረት በተሽከርካሪው አቅም 50% በቻ፣ አካላዊ ርቀት እና PPE መስፈርቶች ይገደባል ፡፡ [የኮሮናቫይረስ የፊት ሽፋን እና ጭምብል መስፈርቶች]

ተግባሪ መሆን የሚችል ከሆነ: የሰራተኛ ደኅንነት እና ጤናን የሚመለከቱ ጉዳዮች በ L&I የ ሙያ ደኅንነት እና ጤና (DOSH) ስር የማስፈጸሚያ እርምጃ ይገዛሉ ፡፡

- አሠሪዎች ስለ ኮቪድ-19 መጠየቅ ይችላሉ [መከላከያ ምክር እና እገዛ] ከ L እና I የሙያ ደህንነት እና ጤና ክፍል (DOSH)
- የሰራተኛ የሥራ ቦታ ደህንነት እና የጤና ቅሬታዎች ለL&I DOSH የደህንነት ጥሪ ማዕከል: (1-800-423-7233) or via e-mail to adag235@lni.wa.gov.
- የ ስምምነት ልምዶችን እንዴት ማክበር እንደሚቻል አጠቃላይ ጥያቄዎች በክልሉ ንግድ ምላሽ ማዕከል በ https://coronavirus.wa.gov/how-you-can-help/covid-19-business-and-worker-inquiries.
- ከአዋጁ 20-25 ጋር የሚዛመዱ ሌሎች ጥሰቶች ሁሉ በማቅረብ ይችላሉ https://bit.ly/covid-compliance.